# የብርሃን ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር የመመስረቻ ጽሁፍ

እኛ የብርሃን ኢንሹራንስ አ.ማ (ከዚህ በኋላ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ “ማህበር/ኩባንያው” እየተባለ የሚጠራውን) ባለአክሲዮኖች በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) እና በኢፌዲሪ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 400(1) መሠረት ታህሳስ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ባደረግነው አራተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከአሁን በፊት የነበረውን የኩባንያውን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በአንድ በማጠቃለል በዚህ የተሻሻለ **“መመስረቻ ጽሁፍ”** እንዲተካ አጽድቀናል።

## ምዕራፍ አንድ ጠቅላላ

### አንቀጽ 1፡ የማህበሩ/የኩባንያው/ ስም

የማህበሩ/የኩባንያው/ ስም ብርሃን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ተብሎ ይጠራል።

### አንቀጽ 2፡ የኩባንያው/የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት

2.1 የኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ፤ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፤ ወረዳ 02፤ የቤት ቁጥር አዲስ፤ ጋራድ ሲቲ ሴንተር፤ 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 01 ስልክ ቁጥር 0114674423፤ ኢሜል insuranceberhan@gmail.com ነው።

2.2 ኩባንያው በኢትዮጵያ በማናቸውም ቦታ እንደአስፈላጊነቱም ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋም ይችላል።

### አንቀጽ 3፡ የኩባንያው/የማህበሩ የተቋቋመበት የንግድ ዓላማና የስራ መስክ

3.1 ኩባንያው/ማኅበሩ የተቋቋመበት የንግድ ዓላማና የሥራ መስክ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ማናቸውንም ዓይነት የጠቅላላ የመድን ሥራዎችን መሥራት፤

ለ. የረጅም ጊዜ ( የሕይወት ነክ መድን) ሥራዎችን መሥራት፤

ሐ. የጠለፋ መድን ዋስትና ሥራዎችን መሥራት፤

መ. በሕግ በተፈቀደው አግባብ አዋጭ በሆኑ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮኖችን መግዛት እና በሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት፤

ሠ.በመድን ስራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1163/2012 ድንጋጌዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት የኩባንያውን የንግድ ዓላማዎች በሚያግዙ እና በሚያጠናክሩ ተጓዳኝ በሆኑ ተግባራት ላይ መሳተፍ፤

3.2 ከዚህ በላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ የመድን ሥራ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲበረታታና የተስተካከለ የኢንሹራንስ ሥራዎች እንዲኖሩ በሚያስችሉ ማናቸውም ዓይነት የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ መሰማራት፤

**አንቀጽ 4 የኩባንያው/የማህበሩ/ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)**

1. የኩባንያው የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል) **ብር 300,000,000.00( ሦስት መቶ ሚሊየን)**ነው። ከዚህ ውስጥ ብር 300,000,000.00( ሦስት ሚሊየን መቶ) ተከፍሏል።
2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ዋና ገንዘብ የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) በሆኑ 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ) መደበኛ አክሲዮኖች ተከፋፍሏል።
3. የኩባንያውን ዋና ገንዘብ/ካፒታል/መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 52-55 እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 442 እና በተከታዮቹ እንዲሁም በአንቀጽ 462 እና በተከታዮቹ መሠረት እንደ አግባቡ ይፈጸማል።

**አንቀጽ 5፡ <u>የኩባንያው/የማህበሩ/ና የባለአክስዮኖች ኃላፊነት</u>**

1. የኩባንያው/የማህበሩ ኃላፊነት ባለው ሀብት መጠን የተወሰነ ይሆናል።
2. የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ በመክፈልና በኩባንያው ውስጥ ባላቸው አክስዮን መጠን የተወሰነ ነው።

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>ስለ አክስዮን፣ የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ</u>**

**አንቀጽ 6፡ <u>የኩባንያው/የማህበሩ/ አክሲዮኖች</u>**

1. የኩባንያው አክስዮኖች የማይከፋፈሉ ናቸው። ብዙ ሰዎች በአንድነት አክስዮኖችን በጋራ የገዙ እንደሆነ አንድ እንደራሴ በመሰየም የባለአክስዮኖች መብትና ግዴታቸው ሳይከፋፈል በአንድነት ተጠቃሚ ይሆናሉ።
2. የኩባንያው/የማህበሩ ባለአክስዮኖች ስም፣አድራሻ ፣ዜግነት፤ የፈረሙትን የአክስዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ጋር በአባሪነት ተያይዟል።
3. ኩባንያው/ማህበሩ የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) የሆነ መደበኛ አክስዮኖች ተብለው የሚመዘገቡና እኩል ዋጋ የሚኖራቸው አንድ ዓይነት አክስዮኖች ይኖሩታል።
4. የኩባንያው/የማህበሩ ባለአክሲዮን መሆን ስለሚችሉ ሰዎች እና አንድ ሰው መያዝ ስለሚችለው ከፍተኛው የአክሲዮን መጠን በመድን ስራ አዋጅ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።
5. ማናቸውም ባለአክስዮን /ፈራሚ ፤ በተናጥል ሆነ ወይም ከባልና ሚስት ጋር በአንድነት ፤ እና ወይም ዕድሜው(ዋ) ከ18 ዓመት በታች ሆኖ በመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና በሥጋ ከሚዛመደው /ከምትዛመደው ግለሰብ ጋር በመሆን ከኩባንያው/ከማህበሩ አክስዮኖች አምስት በመቶ(5%) በላይ መያዝ አይችልም።

6. በማናቸውም ሌላ መድን ሰጪ ኩባንያ ውስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሚያደርገው የአክስዮን መጠን ያለው ባለአክስዮን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት በብርሃን ኢንሹራንስ አ.ማ. ውስጥ አክስዮን መያዝ አይችልም፡፡
7. ኩባንያው የራሱን አክስዮኖች መያዣ በማድረግ ብድር ወይም ዋስትና አይሰጥም ወይም የራሱን አክስዮኖች እንዲገዙ ለሦስተኛ ወገኖች ብድር አይፈቅድም፡፡

## አንቀጽ 7፡ <u>የባለአክሲዮኖች መብት</u>

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እንደዚሁም ሌሎች በየጊዜው የሚወጡ የመድን ስራ እና የባለአክሲዮኖች መብቶች የሚመለከቱ ሕጎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ከዚህ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. በማህበሩ/ኩባንያው/ ባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ/ስብሰባ/ የመካፈል መብት፤
2. በባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ/ስብሰባ በሚወሰነው መሰረት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከሚገኘው የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ በሕግ ለተደነገጉት ሕጋዊ ተቀማጭ ገንዘቦች እና ግዴታዎች የሚውለው ከተቀነሰ በኋላ ከተጣራው ትርፍ የመካፈል መብት፤
3. እያንዳንዱ ባለአክስዮን ባዋጣው ካፒታል መጠን የሚሰላ ሆኖ ኩባንያው ፈርሶ ሥራ በሚያቆምበት ጊዜ ከንብረቱ ሽያጭ ከሚገኘው የተጣራ ገቢ ድርሻውን የማግኘት መብት፤
4. እያንዳንዱ አክስዮን እኩል አንድ ድምፅ የያዘ ሆኖ በያዘው የአክስዮን ብዛት ልክ ድምፅ የመስጠት መብት፤
5. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7(4) ላይ የተጠቀሰው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በሚያወጣው መመሪያ በማናቸውም የባለአክስዮኖች ጉባኤ/ስብሰባ/ ላይ በውክልና ወይም በማህበሩ ተበዳሪዎች የሚሰጥ ድምጽ ላይ ገደብ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 381 ላይ በተደነገገው መሰረት ቃለጉባኤዎችን እና ጠቅላላ ጉባኤዎች/ስብሰባዎች/ ላይ የተገኙ አባላትን ዝርዝር የመመልከት መብት እና የሒሳብ ሚዛንና እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ፤የዳይሬክተሮች ቦርድና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎችና ሌሎች ሰነዶችን የመውሰድ መብት፤
7. ካፒታሉ እንዲጨምር ለማድረግ ሲባል አዲስ የሚወጡትን አክስዮኖች /በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አክስዮኖችን በያዘው/ በያዘችው አክስዮኖች መጠን ድርሻ ላይ ተመስርቶ ለመግዛት የቀደምትነት መብት፡፡
8. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ተደርጎ በቀረበ ጉዳይ ላይ ከድምዳሜ ለመድረስ የሚያስፈልግ ተጨማሪ መረጃ ለጉባኤው እንዲቀርብ የመጠየቅ መብት፤

9. የአክስዮን ድርሻውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሸጥ፤ በስጦታ የመስጠት ወይም በ3ኛ ወገኖች ዘንድ በዋስትና የማስያዝ መብት አለው።
10. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ የመመረጥ ወይም ሌሎችን የመምረጥ መብት አለው።
11. በሕግ የተቀመጡ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም ባለአክስዮን እራሱ ሳይስማማ የአባልነት መብቶቹን ሊነፈግ አይችልም።

## አንቀጽ 8 የባለአክስዮኖች ግዴታና ተጠያቂነት

1. የኩባንያው/ማህበሩ ባለአክስዮኖች ተግባሮች፤ ግዴታዎችና ተጠያቂነት አግባብነት ባላቸው የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000(በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው)፤ እና በተጠቀሱት አዋጆች መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ ይሆናሉ።
2. ማናቸውም ባለአክስዮን ለመክፈል ግዴታ የገባበትን ወይም የፈረመውን የአክስዮን ዋጋ እንዲያስገባ ሲጠየቅ የመክፈል ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 9 ክፍያ ያልተፈጸመባቸው አክስዮኖችን በሚመለከት የሚደረግ ጥሪ

1. የአክስዮኖቹ ባለይዞታዎች የቀድሞ አስተላላፊዎች እና ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ለአክስዮኑ ዋጋ ክፍያ በአንድነትና በተናጥል ኃላፊ ናቸው።
2. አክስዮኖቹ የተሰጡት በአለባ ጥቅም እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለ የአክስዮን ገንዘብ ጥሪው መሰረት ቀሪውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።
3. ማናቸውም ለመግዛት የፈረመ ሰው ወይም ባለአክስዮን የሆነ ሰው የራሱ የሆነውን አክስዮን ያስተላለፈ እንደሆነ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ገና ላልተከፈለው ገንዘብ ኃላፊነት የለበትም።
4. ቀሪውን ያልተከፈለ የአክስዮን ገንዘብ በተወሰነው ቀን ያልከፈለ ባለአክስዮን ላይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 289 ንዑስ አንቀጾች 3-7 የተደነገጉት ተፈጻሚነት አላቸው።

## ***<u>አንቀጽ 10. የባለአክሲዮኖች መዝገብ</u>***

1. ማህበሩ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 274(2) መሰረት የባለአክስዮኖችን ስም፣አድራሻ፣ ዜግነት፣ አክስዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፤ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን፤ ባለአክስዮኖቹ በባለአክስዮንነት የተመዘገቡበትን ቀን ያካተተ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ማዘጋጀትና በዋናው መ/ቤት መያዝ አለበት። መዝገቡ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል።

2. ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ፈቃድ ያለው ማንኛውም አባል በማህበሩ ዋና መ/ቤት ወይም በዋና የስራ ቦታው ላይ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ወቅት መዝገቡን በግልፅ ለመመርመር ይችላል።

## ***አንቀጽ 11. የአክሲዮን ዝውውር***

1. የአክስዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በሥራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ሳይቃረን ያለምንም ገደብ ሊዘዋወር ወይም ሊተላለፍ ይችላሉ።
2. ማንኛውም የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በጽሑፍ መስፈርና የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያፀድቀው ፎርም መሠረት መሆን አለበት።
3. ማንኛውም የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ መመዝገብ ያለበት ሲሆን በመዝገቡ ውስጥ እስካልሰፈረ ድረስ ውጤት አይኖረውም።
4. ማንኛውም ባለአክስዮን ሕይወቱ በሚያልፍበት ጊዜ በሕጉ መሰረት ሕጋዊ ወራሾቹ በባለአክስዮኑ ፈንታ የሚተኩ ይሆናል።

## **አንቀጽ 12 የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ**

1. የኩባንያው/ማህበሩ ዓመታዊ ትርፍ ለባለአክስዮኖች የሚከፋፈለው ለትርፍ ክፍያው መከፈል ምክንያት በሆነው በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ወቅት ባላቸው የተከፈለ አክስዮን ይዞታ መጠን የተከፈለበትን ቀን ታሳቢ በማድረግ ነው።
2. ከተጣራ ትርፍ ላይ የትርፍ ድርሻ ክፍያ የሚደረገው ማንኛውም ግብር፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሒሳብና ጠቅላላ ጉባኤው/ስብሰባው/ በየጊዜው የሚያጸድቃቸው የዚሁ ዓይነት መጠባበቂያ ሒሳቦች ፣ ከተቀነሱ በኋላ ነው። በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ቀሪው ገንዘብ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 12(1) መሰረት ይከፋፈላል።
3. የትርፍ አከፋፈል የኩባንያው/ማህበሩ ኦዲተሮች በመረመሩትና የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ባፀደቀው የተጣራ ትርፍ ድምር ላይ በመመስረት ተፈጻሚ ይሆናል።
4. ለክፍፍል የሚሆነው የተጣራ ትርፍ ከሒሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ ያለፈው ዓመት ኪሣራዎችና ማናቸውም የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያዎች (ለዳይሬክተሮች ቦርድና ለሌሎችም አካላት የተፈቀዱ ወጪዎችና ክፍያዎች) ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ነው።
5. ተቀባይነት ካገኘው የሒሳብ ሚዛን ውጭ የሚደረግ የትርፍ ድርሻ ክፍያ እንደጉድለት ተወስዶ በሕግ ያስቀጣል።
6. የትርፍ ክፍያው ቀንና ዝርዝር ሁኔታዎች በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።

## **አንቀጽ 13 ለመሥራቾች የተመደበ የትርፍ ድርሻ**

ማህበሩ/ኩባንያው ትርፍ ካገኘበት የመጀመሪያ ዓመት አንስቶ ለማህበሩ መሥራቾች በሂሳብ ሚዛን ውስጥ ከሚታየው የተጣራ ትርፍ ላይ በቅድሚያ ለሦስት/3/ ተከታታይ ዓመታት በምስረታው ወቅት በገዙት የተከፈለ የአክስዮን ዋጋ ላይ የ10% ድርሻ የማግኘት መብት የነበራቸው ሲሆን ይህም ኩባንያው/ማህበሩ ትርፍ ማስመዘገብ ከጀመረ በኋላ በነበሩት ሦስት ዓመታት የመስራቾች ጥቅም ክፍያ ተፈጽሞ ተጠናቋል።

## አንቀጽ 14 የኩባንያው የአስተዳደር አካላት

1. የኩባንያው የአስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የባለአክስዮኖች ጉባኤ

ለ. የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሐ. ዋና ሥራ አስፈጻሚ

መ. የማኅበር ጸሃፊ

ሠ. የውጭ ኦዲተር /ኦዲተሮች

2. ከዚህ በላይ የተመለከቱት የማህበሩ የአስተዳደር አካላት ሥልጣን፤ ተግባርና ኃላፊነት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች እንዲሁም በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሰረት ይሆናል።

## ምዕራፍ አራት

## የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

## አንቀጽ 15፡ <u>ጠቅላላ ደንቦች</u>

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም ባለአክሲዮኖች ሊሳተፉ የሚችሉበት የማህበሩ/ኩባንያው የበላይና ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ሲሆን የኩባንያውን ተግባራት በበላይነት ለመምራት ሙሉ ስልጣን አለው።
2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው በአካል በመገኘት ወይም አስተማማኝ በሆነ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊደረግ ይችላል። አስተማማኝ የሆነ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚባለው የተሰብሳቢዎችን ማንነት መለየት፣ ተሰብሳቢዎች በአንድ ጊዜ መሳተፍ፣ ድምጽና ምስል ሳይቆራረጥ ማስተላለፍ፣ በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ አስተያየትና ድምጽ መስጠት እና የሚሰጠው ድምጽ መቁጠር የሚያስችል ሲሆን ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በፅሑፍ ወይም ማንነታቸውን ለመለየት በሚያስችል ኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለፅ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ።

## አንቀጽ 16 የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣን

1. የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ/ኩባንያው የበላይ አካል ሆኖ ከባለአክስዮኖች መካከል የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይመርጣል።
2. በሁሉም ባለአክስዮኖች ስም በስብሰባ ባልተገኙት፤ ባልተስማሙት ፤ ለመምረጥ ባልቻሉት ወይም የመምረጥ መብት በሌላቸው ስም ጭምር ይወስናል።

3. የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የራሱን ተግባራት የመምራት ሥልጣን ያለው ከፍተኛው የማህበሩ ባለሥልጣን ነው። ይህ አጠቃላይ ሀሳብ በምንም ዓይነት ሳይቀነስ ማህበሩ የሚያካሒደውን የንግድ ሥራ በሚገዛው ሕግ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 18 እና 19 የተጠቀሱት ሥልጣኖች አሉት።
4. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ባለአክስዮኖች በጉባኤው ባይካፈሉ ባይስማሙ ድምፅ መስጠት ባይችሉ ወይም መብት ባይኖራቸውም በሁሉም ላይ ይጸናሉ።

**አንቀጽ 17 ልዩ ልዩ ዓይነት ስብሰባዎች/ጉባኤዎችና የጉባኤው ጥሪ**

1. ጠቅላላ ጉባኤዎች / ስብሰባዎች/ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ናቸው።
2. መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ/ስብሰባ/ በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኦዲተሮች ጠሪነት ሊደረግ ይችላል።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወይም በኦዲተሮች ሲጠራ ወይም ቢያንስ ከማህበሩ ካፒታል/ዋና ገንዘብ/ 10% የሆነውን የሚወክሉ ባአክስዮኖች ሲጠይቁ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።
4. እንደዚሁም ጠቅላላ ጉባኤዎች/ስብሰባዎች/ እንደሁኔታው በብሔራዊ ባንክ ወይም በሂሳብ አጣሪዎች ወይም በፍ/ቤት ሹም ሊጠሩ ይችላሉ።
5. የባለአክስዮኖች ጉባኤ የሚመራው በዳሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፤ እሱ በማይኖርበት ጊዜ በዳሬክተሮች ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ ይሆናል። እንዲሁም ስብሰባው የተጠራው በኦዲተሮች ፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በሒሳብ አጣሪ ከሆነ ስብሰባውን በጠራው አካል ይመራል።

**አንቀጽ 18፡ <u>መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ</u>**

1. በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በኦዲተሩ/ሮቹ ጥሪ ከበጀት አመቱ መዝጊያ በኋላ ባሉት በ4 ወራት ውስጥ በየአንዳንዱ በጀት አመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መካሄድ አለበት። ይሁን እንጂ ጠቅላላ ጉባኤውን የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በ4 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤው መደረግ አለበት።
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል።
3. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፤ አግብብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎችና በሥራ ላይ ባሉት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተጠቀሱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

3.1 የማህበሩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ፣ የዳይሬክተሮችና የኦዲተሮች ሪፖርቶች በመመርመር እንዲጸድቁ ወይም እንዲሻሻሉ ወይም ውድቅ እንዲሆኑ ይወስናል።
3.2 በትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ይወስናል።
3.3 የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና ምርጫ አፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፤ ያሻሽላል።

3.4 ከአባላቱ መካከል የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፤ ይሽራል፤ የስራ ዋጋቸውን ይወስናል።

3.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፤ የስራ ዋጋቸውን ይወስናል።

3.6 የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፤ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜያቸውንና የስራ ዋጋቸውን ይወስናል።

3.7 ማህበሩ የግዴታ ወረቀቶችን እንዲያወጣ መፍቀድና ከዚያም ጋር በተያያዘ የሚሰጡትን መያዣዎች ይወስናል።

3.8 ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከተመደቡት ጉዳዮች በቀር በሌሎች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስንባቸው ጉዳዮች ሁሉ ይወስናል።

## አንቀጽ 19፡ <u>አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ</u>

1. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።
2. ሌሎች በሕግ ተለይተው የተሰጡ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   - 1.1 የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ማጽደቅ፤ ማሻሻል፤
   - 1.2 የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ ወይም መቀነስ፤
   - 1.3 የማህበሩን ዜግነት መለወጥ፤
   - 1.4 ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ዓላማዎቹ እንዲለወጡ፣ ወደ ሌላ አይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም ከሌላ ማህበር ጋር እንዲዋሃድ መወሰን፤

## አንቀጽ 20 ፡ <u>ምልዓተ ጉባኤ እና የድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም የማህበሩ ጉባኤ ውሳኔ ማሳለፍ የሚችለው ምልዓተ ጉባኤው የተሟላ ሲሆንና በጉባኤው በተገኙት ባለአክሲዮኖች የአብላጫውን የድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው።
2. ለድምጽ ብልጫ አቆጣጠር ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተፃፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም።
3. ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቶ እና አስፈላጊው የድምጽ ብልጫ አግኝተው የሚተላለፉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በስብሰባው ያልተካፈሉ፣ ድምጸ ተአቅቦ ባደረጉ፣ በሃሳብ በተለዩ፣ ድምጽ ለመስጠት ችሎታ የሌላቸው ወይም ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ ባለአክሲዮኖች ጨምሮ በሁሉም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
4. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ በአብላጫ ድምፅ ላይ ተመስርቶ ውሳኔዎችን መመርመርና ማሳለፍ አለበት፡: ይህም የሚሆነው፡-
   - ሀ. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ(የተፈረመ የአክስዮን መጠን) አንድ  አራተኛ የሚወክሉ ባለአክስዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ፤ ወይም

ለ. በመጀመሪያው ጥሪ ላይ ምልዓተ ጉባኤ ካልተገኘ በ2ኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ ( የተፈረመ የአክስዮን መጠን)ግምት ውስጥ ሳይገባ ፤

5. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው፡-

ሀ. በመጀመሪያው ጥሪ ከ1/3ኛ ያላነሱ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው የሁሉም አክስዮኖች ባለቤቶች ሲገኙ፡ ወይም በእንደራሴ ሲወከሉ።

ለ. በሁለተኛው ጥሪ ከ1/4ኛ ያላነሱ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው የሁሉም አክስዮኖች ባለቤቶች ሲገኙ ወይም በእንደራሴ ሲወከሉ፤

ሐ. በሦስተኛው ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክስዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (የተፈረመ የአክስዮን መጠን) ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለአክስዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው።

6. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የጸና የሚሆነው በጉባኤው የተገኙት ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክስዮኖች ከወከሉትዋና ገንዘብ(የተፈረመ አክስዮን መጠን) ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን በሚወክሉት ድምፅ ከተደገፈ ነው።
7. አስቸኳይ ጉባኤው የማህበሩን/የኩባንያው/ ዜግነት መለወጥ የሚችለው ወይም በነባር አክስዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የማህበሩን ዋና ገንዘብ(ካፒታል) ማሳደግ የሚችለው ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸውን ባለአክስዮኖች ሙሉ ድጋፍ ያገኘ እንደሆነ ነው።
8. ሕግን ፤ የማህበሩን መመሥረቻ ሠነድን በመከተል የተደረጉት የስብሰባው ውሳኔዎች በስብሰባው ያልተገኙትን ወይም በሃሳብ ያልተስማሙትን አባላት ጨምሮ ሁሉንም ያስገድዳል።

## አንቀጽ 21 የጠቅላላ ስብሰባዎች/ጉባኤዎች የማስታወቂያ ጊዜ

1. ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች የሚደረግ ጥሪ ስብሰባው እንዲደረግ ከተመረጠበት ቀን ቢያንስ ሃያ አራት ቀናት አስቀድሞ በሃገራችን ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባላው ባለው ጋዜጣና በማህበሩ ድረ ገጽ ላይ መተላለፍ /መውጣት አለበት።
2. ማህበሩ የጉባኤውን ጥሪ በኢሜል፤ በተንቀሳቃሽ ስልክ በሚላክ አጭር የጽሁፍ መልዕክት፤ በደብዳቤ ወይም ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያስተላልፍ ይችላል።
3. ኩባንያው/ማህበሩ/ አስፈላጊ ሆኖ ከአገኘው የጥሪ ማስታወቂያውን በመገናኛ ብዙኃን ሊያደርገው ይችላል።

## አንቀጽ 22 ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ የሚጠራ መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ

አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ/ስብሰባ/ ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ የተነሳ ሥራውን ማካሄድ ካልቻለ ለመጀመሪያው ጉባኤ/ስብሰባ/ በተደረገው ዓይነት ሁለተኛ ስብሰባ ይጠራል።

## አንቀጽ 23 ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ የተነሳ የሚጠራ አስቸኳይ ጠቅላላ ስብሰባ

ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ የተነሳ አንድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መደረግ ሳይችል ሲቀር ለሁለተኛ እና ካስፈለገም ለሦስተኛ ጉባኤ ሁለት የጋዜጣ ላይ የጥሪ ማስታወቂያዎች በመጀመሪያውና በሚቀጥለው መሐል አንድ ሳምንት በመተው በሚደረግ ጥሪ አማካኝነት የጉባኤው የማስታወቂያ ጊዜ ይገለጻል። በተጨማሪም በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ በሚገኝ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦታና በኩባንያው ድረ-ገጽ እንዲለጠፍ ይደረጋል።

## አንቀጽ 24 ጉባኤዎችን በውክልና መሳተፍ

1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ጠቅላላ ጉባኤውን በወኪል አማካኝነት መሳተፍ ይችላል። ሆኖም ማንኛውም ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን ወኪል ሆኖ የሚሰጠው ድምጽ መጠን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ይሆናል። ባለአክሲዮኑ በጉባኤው ላይ ወኪል እንዲገኝ ካደረገ እራሱ ለመሳተፍና ድምጽ ለመስጠት አይችልም።
2. የውክልና ስልጣን ቅጽ ይዘትና ውክልናው የሚቀመጥበት ጊዜና ቦታ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል። ሆኖም የውክልናው ቅፅ በወካዮች ተሞልቶ የሚቀመጥበት የጊዜ ገደብ ስብሰባው ከሚጀመርበት ጊዜ ከሶስት ቀን በፊት መጠናቀቅ አይችልም።
3. አንድ ባለአክስዮን በአንድ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ/ጉባኤ/ ተወካይ የሚመድበው በጽሁፍ በተዘጋጀ ሠነድ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 25 የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ

1. በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ በጉባኤው ላይ የተገኙ ባለአክስዮኖችን የሚያስረዳ የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ መኖር አለበት። ዝርዝሩ በስብሰባው የተገኙትን ባለአክስዮኖች ወይም በእንደራሴ የተወከሉት ባለአክስዮኖች ስምና አድራሻቸውን እና እያንዳንዱ ባለአክስዮን በማህበሩ ውስጥ ያለውን የአክስዮን መጠንና የሚሰጠውን የድምፅ ቁጥር ማሳየት አለበት።
2. በስብሰባው ላይ የተገኙት ባለአክስዮኖች የተመዘገቡበት የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በጉባኤው በተገኙት ባለአክስዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው የተፈረመበትና ስለመሆኑ በማህበሩ ፀሐፊ መረጋገጥ አለበት።

## አንቀጽ 26 የጥቅም ግጭት

1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ስለራሱ ወይም ሦስተኛ ወገንን ወክሎ ከኩባንያው ጋር የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ድምጽ መስጠት አይችልም።
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የራሳቸውን ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም በማህበሩና በራሳቸው ጥቅም መካካል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ድምጽ መስጠት አይችሉም።

3. ምልዓተ ጉባኤ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 እና 2 ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ አክሲዮኖች ከቁጥር ውስጥ ይገባሉ።
4. በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ፤ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው በባለክሲዮኖች ጉባኤ ድምጽ በነፃነት የመስጠት የባለአክሲዮኖች መብት አይገደብም።

**አንቀጽ 27 ቃለጉባኤ**

1. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች  በቃለ ጉባኤ ይመዘገባሉ። በቃለ ጉባኤ መዝገብ ላይ ተጽፈው በጉባኤው ላይ የተገኙት የዳይሬክተሮች አባላትና የማህበሩ ጸሃፊ ይፈርሙበታል። በዚህ ሁኔታ በመዝገቡ ላይ የተጻፈው ትክክል ስለመሆኑ በኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ/ሊቀመንበር/ ወይም በሁለት ዳይሬክተሮች የተረጋገጠ መሆን አለበት።
2. ቃለጉባኤዎች ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት/መያዝ/ አለባቸው።

ሀ. የጉባኤውን ጥሪ አደራረግ

ለ. ስብሰባው የተደረገበት ቦታና ቀን

ሐ. አጀንዳዎቹን

መ. በጉባኤው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም

ሠ. በስብሰባው ላይ የተገኙ አክስዮኖችን ብዛትና የምልዓተ ጉባኤውን ቁጥር

ረ. ለጉባኤው የቀረቡትን ሰነዶች

ሰ. የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ

ሸ. የተሰጡትን ድምፆች ውጤት እና

ቀ. ጉባኤው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች

3. ምልዓተ ጉባኤ ሳይገኝ ሲቀር ሰብሳቢው ይህንኑ በቃለ ጉባኤው መዝገብ ላይ ያሰፍራል።
4. የቃለ ጉባኤዎች ቅጅዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ/ሊቀመንበር/ ወይም በሁለት ዳይሬክተሮች ይረጋገጣሉ።

**ምዕራፍ አምስት**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

**አንቀጽ 28 የዳይሬክተሮች ስያሜ**

1. ማህበሩ/ኩባንያው ከባለአክሲዮኖች መካከል በጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጡ ዘጠኝ አባላት ባሉት አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል።

2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለመሆን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ የእድሜ፣ የትምህርት፣ የስራ ልምድ፣ የስነምግባርና ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ከተመረጡበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ የሥራ ጊዜውን የጨረሰ ዳይሬክተር ለሁለተኛ ጊዜ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ሰው በራሱም ሆነ በውክልና ከስድስት ተከታታይ አመታት በላይ በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችልም፡፡ ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤው የስራው ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሶስተኛ ያልበለጡትን ለሦስተኛ ዙር በቦርድ አባልነት እንዲሰሩ ሊመርጣቸው ይችላል፡፡
5. ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡ እንደዚሁም ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑስ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡
6. በማንኛውም ምክንያት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከተጓደለ እና የቀሩት አባላት 50% ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የተጓደሉትን ዳይሬክተሮች የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ባገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት በመተካት ለመሾም ይችላሉ፡፡ የምትክ ዳይሬክተሮች ሹመት እንዲጸድቅ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. የተተኩት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሹመት እንዲፀድቅ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤውም ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን ሊሾም ይችላል፡፡ ሹመታቸው በጠቅላላ ጉባኤው ሳይፀድቅ ቢቀር እንኳን በሹመታቸው ጊዜ ያከናወኑት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
8. በማናቸውም ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከአምስት በታች ከሆነ አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ ቦርዱ በ30 ቀናት ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት፡፡

## **አንቀጽ 29 <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ/ኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የማህበሩን ስራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
2. ማህበሩ ጤናማ የፋይናንስ አስተዳደር፣ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈጸም አቅም ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
3. የኩባንያውን የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች ይወስናል፡፡ ማህበሩ የሚያደርገውን ኢንቨስትመንት በፖሊሲው መሰረት ያጸድቃል፡፡

4. ትርፋማ በሆኑ የንግድ ድርጀቶች ውስጥ ማህበሩ አክስዮኖችን እንዲገዛ፤ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ያለውን አክስዮን እንዲሸጥ፤ እንዲሁም አዲስ አክስዮን ማህበራትን ከሌሎች ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር በመሆን እንዲያቋቁም ይወስናል፡፡
5. የማህበሩን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
6. የማህበሩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡ በየበጀት ዓመቱ የሚከፈቱ የቅርንጫፎችን ቁጥር ይወስናል፡፡
7. የማህበሩን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሾማል፤ ከስራ ያሰናብታል፡፡ ሥልጣኑንና ተግባሩን፤ የቅጥር ሁኔታውን፤ ደመወዙንና ጥቅማጥቅሞቹን ይወስናል፡፡
8. በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚቀርበውን የኩባንያውን ድርጅታዊ መዋቅር፤ የሰራተኞች ደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም፤ ልዩ ልዩ ማኑዋሎችን፤ የሰው ኃይል ፍላጎትና ድልድል እንዲሁም የኩባንያውን ሥራ አመራር ፖሊሲና መመሪያዎችን ያጸድቃል፡፡
9. የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት የማህበሩን ምክትል ዋናሥራ አስፈጻሚ/ዎች፣ የመምሪያና የአገልግሎት ኃላፊዎችን እንዲሁም የማህበሩን ጸሐፊ ሹመት፤ ምደባና ስንብት ያፀድቃል፡፡
10. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎች በወቅቱ በማከናወን የማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ትርፍና የኪሳራ ሂሳብ ያዘጋጃል፣
11. የማህበሩን የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ይጠራል፤ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጉባአው ያቀርባል፡፡
12. በሕግና በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የመጠባበቂያ ሒሳቦችን ያቋቁሟል፡፡
13. የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የባለአክሲዮን መዝገብ፣ የዳይሬክተሮች መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
14. የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ ጥቆማና ምርጫ አፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡
15. የማህበሩን የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡
16. ገንዘብ ለመበደርና በኩባንያው ስም የብድር ስምምነቶችና ውሎችን ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዲፈርም ለመፍቀድ ይችላል፡፡
17. የግዴታ ወረቀቶችን ያወጣል ከዚያም ጋር የተያያዙትን ዋስትናዎች ያፀድቃል፡፡
18. የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ማህበሩ የሚንቀሳቀስ ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን እንዲገዛ፤ እንዲሸጥ፤ የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ እንዲከራይ ወይም እንዲያከራይ መወሰን ይችላል፡፡
19. ለማህበሩ ስራ አላማዎች ግብ መምታት አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
20. ገንቢ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ሃሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

21. የማህበሩ ካፒታል እንዲጨምር ወይንም እንዲቀንስ ለጠቅላላ ጉባኤ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
22. ማህበሩ በሚያዘጋጃቸው የውስጥ ደንብ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ከተሰጡት ገደቦች በላይ የሆኑ ግዥዎችን መርምሮ ያፀድቃል፡፡
23. በቅድሚያ በዝርዝር የተዘጋጀን ደንብ መሰረት በማድረግ በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞች ከረዥም ጊዜ አገልግሎት በኋላ ከሥራ ሲሰናበቱ ስጦታ በአይነት ወይም በገንዘብ መሸለም ይችላል፡፡
24. የአገሪቱን ሕግ መሰረት በማድረግ ማህበሩ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል በበጎ አድራጎት ተግባር ለተሰማሩ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ወይም ለፌዴራል ወይም ክልላዊ መንግስት የአይነት ወይም የገንዘብ ስጦታ ለማድረግ ይችላል፡፡
25. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 473 እና በተከታዮቹ በተደነገገው መሰረት ኩባንያው እንዲፈርስ ወይም ሒሳቡ እንዲጣራ ሲወሰን፤ ለተግባራዊነቱ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
26. በሕግ ፤ በዚህ የመመስረቻ ሰነድ ወይም በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤዎች ለማህበሩ ሌላ አካል /ሌሎች አካሎች/ በተለይ ከተሰጡ ሥልጣኖች በስተቀር ፤ የማህበሩ ድርጅታዊ ሥልጣኖች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ናቸው፡፡
27. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰኑ ስልጣኖቹን በዝርዝርና ግልጽ በሆነ መልኩ ለማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## **አንቀጽ 30 የዋስትና አክስዮኖች**

ዳይሬክተሮች ሥራቸውንና ተግባሮቻቸውን በትክክልና በሚገባው አሠራር ለመወጣታቸው ዋስትና እንዲሆን እያንዳንዳቸው 20/ሃያ/ የተመዘገቡ አክስዮኖች በማህበሩ ዘንድ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡ እነዚህ አክስዮኖች ባለቤቶቹ ዳይሬክተርነታቸውን እስካለቀቁና ለማህበሩ ያለባቸውን ኃላፊነት በሙሉ እስካልተወጡ ድረስ አይለቀቁም፡፡

## **አንቀጽ 31፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ የቦርዱ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ከአባላቱ መካከል በአብላጫ ድምጽ ይመረጣሉ፡፡
2. የቦርድና የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም እርሱ/እርሷ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢ ወይም እርሱ/እርሷ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ በሥራ ቀደምትነት ባለው ዳይሬክተር ሁለቱም ከሌሉ በስብሰባው በሚሾመው ይመራሉ፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ ዋና መ/ቤት ወይም ሰብሳቢው/ዋ/ በሚመርጡት ቦታ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለማህበሩ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ይሰበሰባል፡፡

## ***አንቀጽ 32*** **የዳይሬክተሮች /የቦርድ አባላት/ ግዴታ፤ ተግባርና ኃላፊነት**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማህበሩን የበለጠ ስኬታማ ያደርጋል ብለው በቅን ልቦና ያመኑበትን እርምጃ መውሰድ አለባቸው። የመላው ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሥራት ይኖርባቸዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 32(1) ሥር የተመለከተውን ኃላፊነት በሚወጣበት ጊዜ አንድ ዳይሬክተር የማህበሩን የረጅም ጊዜ ጥቅም፣ የሠራተኞች ጥቅም፣ ከማህበሩ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸውን ሰዎች ጥቅም፣ የማህበሩ ሥራ በማህበረሰቡ እና በአካባቢው ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኃላፊነቱን በጥንቃቄ፣ በብልሀትና በትጋት መወጣት አለበት። በጥንቃቄ ወይም በትጋት ጉድለት በማህበሩ እና በባለአክሲዮኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ዳይሬክተሩ ተጠያቂ ይሆናል።
4. ጠቅላላ ጉባዔው ካልፈቀደ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በራሳቸው ወይም በሦስተኛ ወገኖች ስም ከማህበሩ ጋር መወዳደር ወይም ተወዳዳሪ በሆኑ የንግድ ማህበራት ውስጥ አባል መሆን አይችሉም።
5. የአንድ ማህበር ዳይሬክተር ከሚመራው ማህበር ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ራሱን ማራቅ አለበት።
6. እያንዳንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በራሱ እና በማህበሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችልን ማንኛውንም ሁኔታ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።
7. በተለይም ከማህበሩ ጋር ሊደረግ የታሰበ ወይም የተደረገ ውል ወይም ሌላ ዓይነት ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የቦርድ አባሉን ጥቅም የሚነካ ከሆነ አባሉ ስለጥቅሙ ባሕሪ እና መጠን ለተቀሩት ዳይሬክተሮች የተሟላ መግለጫ መስጠት አለበት።
8. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀፅ 32(6) እና 32(7) ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም መግለጫ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ስለመኖሩ እንደታወቀ ወዲያውኑ መቅረብ ይኖርበታል።
9. አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ በሦስተኛ ወገን ስጦታም ሆነ ሌላ ዓይነት ጥቅም የተሰጠው እንደሆነ የጥቅሙ ተጋሪ ያልሆኑ ዳይሬክተሮችን ወይም የማህበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ሳያስፈቅድ መቀበል አይችልም።

## ***<u>አንቀጽ 33 ፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ</u>***

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እሱ በማይኖርበት ጊዜ በም/ሰብሳቢ ፤ወይም በሦስት የቦርድ አባላት ጥሪ ሊደረግ ይችላል።
2. የቦርድ ስብሰባዎች ጥሪ ለሁሉም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባው ከመደረጉ አምስት ቀን በፊት ከአጀንዳው ጋር መተላለፍ ይኖርበታል። ሆኖም ቦርዱ ቀደም ብሎ የተላለፈና ቀጠሮ የያዘለት ጉዳይ ከሆነ ጥሪ ማስተላለፍ አስፈላጊ አይሆንም።
3. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት ለመገኘት የሚችል ሲሆን የቦርድ አባል ሆኖ ካልተመረጠ በስተቀር በቦርድ ስብሰባ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት የለውም።

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ሊደረጉ የሚችሉት ከቦርድ አባላት አብዛኛዎቹ ሲገኙ ነው። የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚተላለፈው በተቻለ መጠን በሙሉ ድምፅ ይህም ካልሆነም በድምጽ ብልጫ *ነው። ድምጽ እኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የሚደግፈው* ውሳኔ ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል።
5. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት ወይም የቦርዱ ሰብሳቢ በሚወስነው ሌላ ቦታ ይሰበሰባል።
6. ለባለአክስዮኖችም ሆነ ለሦስተኛ ወገኖች የሚሰጡ የቦርድ ቃለ ጉባኤ ቅጅዎች ትክክለኛነት በማህበሩ ጸሃፊና በኩባንያው ማህተም መረጋገጥ ይኖርባቸዋል።
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ለማውጣትና ሥራ ላይ ለማዋል ይችላል።
8. ማናቸውም ዳይሬክተር አንድ ድምጽ የመስጠት መብት አለው።
9. በቦርድ ስብሰባ ያልተገኘ ዳይሬክተር የሚወክለው ሌላ ዳይሬክተር ሊሰይም ይችላል። ሆኖም አንድ ዳይሬክተር ከአንድ ውክልና በላይ መቀበል አይችልም።
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን ለማድረግ አጋዥነቱ አስፈላጊ ነው ብሎ በገመተ ጊዜ ሁሉ በባለሙያዎች ምክር ሊረዳ ይችላል።
11. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው በተገኙ አባላትና በማህበሩ ጸሃፊ መፈረም አለባቸው። ቃለ-ጉባኤው በቃለ-ጉባኤ መዝገብ መያዝ አለበት።የውሳኔዎች ቅጅዎች በሙሉ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይፈረማሉ።
12. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ በቪዲዮ ኮንፈረስ/በዙም/ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ መሳተፍ ይችላሉ።
13. የመገናኛ ዘዴው የተሰብሳቢዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ የተሳታፊዎችን ድምጽ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹን በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት።
14. በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሳተፉት የቦርድ አባላት ድምጻቸውን በቃል መስጠት ይችላሉ።
15. ከቦርዱ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ቢያንስ **1/3ኛ( ሦስት አባላት)** በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በስተቀር በዚህ ደንብ አንቀጽ 33(7)መሰረት በተደረገ ሰብሰባ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም።

## አንቀጽ 34 ፡ <u>የዳይሬክተሮች አበልና የሥራ ዋጋ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መምሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእያንዳንዱ ዳይሬክተር የሚከፈለው ማናቸውም አበል ወይም ጥቅም በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

## አንቀጽ 35፡ <u>ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ</u>

1. ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የዋና ሥራ አስፈጻሚን፣ የኦዲተሮችን እና የማህበሩ ፀሐፊ እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 306(6)(ለ)(ሐ)(ረ) የተጠቀሱ ሰዎች የግል ሁኔታ፣ ሙያቸውን፣ በሌሎች የንግድ ማህበራት ወይም ድርጅቶች ውስጥ ያላቸውን ጥቅም፣ ስራ፣ የቦርድ አባልነት

ወይም ሌላ ኃላፊነት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በዝርዝር የሚያሳይ መዝገብ በዋና መሥሪያ ቤት ይይዛል።

2. የቦርድ ዳይሬክተሩ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስምና የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻ በመዝገቡ ይካተታል።
3. በመዝገቡ የሰፈሩትን ዝርዝሮች በሙሉና እንዲሁም በዝርዝሮቹ ላይ የተደረጉ ለውጦች ሁሉ መዝገቡ ላይ በሰፈሩ ወይም ለውጡ በተደረገ በ15 ቀን ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ለንግድ ሚኒስቴር ይላካል።
4. ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል ማናቸውም በተመለከተ በመዝገቡ የሰፈሩ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ካለ ይህንኑ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት።

አንቀጽ 36 **ከዳይሬክተርነት ስለመነሳት**

1. **በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013፤** በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው)፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፤ እንዲሁም በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም ሌሎች ሕጋዊ ሰነዶች ላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከአባልነት ሊነሳ/ሊወገድ ይችላል።

ሀ. በጠቅላላ ጉባኤ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውሳኔ

ለ. አንድ ዳይሬክተር ለሥራው ተገቢ ላለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖር ፣ ይኸውም የማህበሩን ሥምና ጥቅም በሚጎዳ ተግባር መሰማራቱ በተቀሩት ዳይሬክተሮች ታምኖበት በዳይሬክተሮች የሥራ ባልደረቦቹ/ቿ በሙሉ ሥራውን እንዲለቅ/ እንድትለቅ/ በጽሁፍ ሲጠየቅ/ስትጠየቅ/

ሐ. ዕምነት በማጉዳል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተላለፈበት

መ. ዳይሬክተሩ በራሱ ፍላጎት በጽሁፍ የዳይሬክተርነቱን ኃላፊነት/ሥራ/ ለመተው የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ፣

ሰ. ሲከስር ወይም ዕዳ መሸፈን ሲሳነው ወይንም ዕዳውን አለመክፈሉ አንዳይታወቅ ከአበዳሪዎቹ/ቿ ጋር ከተመሳጠረ/ች

ረ. የአዕምሮው ጤና መታወክ ያገጠመው በመሆኑ ሥራውን በአግባቡ መወጣት ካልቻለ

ሠ. በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ቦርዱ ከሚያደርጋቸው ስብሰባዎች መካከል ቢያንስ 75% በአካል ለመገኘት ያልቻለ የቦርድ አባል በጠቅላላ ጉባኤው ተቀባይነት ያለው በቂ ምክንያት ካላቀረበ በስተቀር ወዲያውኑ ከቦርድ አባልነት ይወገዳል።

ሸ. ዳይሬክተሩ ሥልጣኑን ከማህበሩ ጥቅም ጋር በሚጋጭ አኳኋን በመገልገል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያልተገባ ጥቅም ማግኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 297/2/ መሰረት ከዳይሬክተርነት መውረድ አለበት።

2. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቦርድ አባላት ለሚፈጽሙት የሥነሥርዓት ጥሰት ቦርዱ በሚያጸድቀው የዳይሬክተሮች ቦርድ የአሠራር መመሪያ መሰረት ከሚከፈላቸው ወርሐዊ ወይም ዓመታዊ ክፍያ

ላይ እንዲቀነስባቸው መወሰን ይችላል። በተጨማሪም የሥነ ሥርዓት ጥሰቱ እየቀጠለ የሚሔድ ከሆነም ቦርዱ ከቦርድ አባልነት ሊያነሳው ይችላል።

ምዕራፍ ስድስት

የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ኃላፊነት

## አንቀጽ 37 የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት

ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይኖረዋል። ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል።

## አንቀጽ 38 የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የኩባንያውን መደበኛ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ሙሉ የሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን አለው። ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ዋና ሥራ አስፈጻሚው የኩባንያው የበላይ ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በዳይሬክተሮች ቦርድ አጠቃላይ አመራር መሰረት የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተለይም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1.1 የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤና የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በተግባር ያውላል።

1.2 የኩባንያውን የተለያዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችና ስትራቴጂዎች በማዘጋጀት የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያጸድቃቸው ያደርጋል። ሲፈቀዱም በሥራ ላይ ያውላል።

1.3 የኩባንያውን ድርጅታዊ መዋቅር ያዘጋጃል፤ በቦርድ ሲጸድቅ ስራ ላይ ያውላል።በፀደቀው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት አስፈላጊ የሆኑ የኩባንያውን ሠራተኞች በኩባንያው ፖሊሲዎችና መመሪያዎች መሰረት ይቀጥራል። ያስተዳድራል። ያሰናብታል። ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን ለዳይሬክተሮች ቦርድ በማቅረብ ያስወስናል።

1.4 ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስፈጻሚና ለቦርዱ የሆኑትን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን፤ መምሪያና የአገልግሎት ኃላፊዎችን ሹመትና ቅጥር እንዲያጸድቅ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል።

1.5 የኩባንያውን ዓመታዊ ዕቅዶች ፤ የሥራ ፕሮግራሞችና በጀት አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲጸድቅ ያቀርባል። ከጸደቀም በኋላ በሥራ ላይ ያውላል።

1.6 የኩባንያውን የባንክ ሒሳብ ይከፍታል። ያንቀሳቅሳል። የተከፈቱትን ሒሳቦች በየሩብ ዓመቱ ለቦርድ ሪፖርት ያቀርባል።

1.7 የማህበሩን የሒሳብ አያያዝ ይመራል። ይቆጣጠራል። የኩባንያውን የአስተዳደርና የሒሳብ መዛግብትና ሠነዶች በሚገባ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል።

1.8 የኩባንያውን ወርሐዊ፤ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የሥራ ዕንቅስቃሴ ሪፖርቶች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፡፡

1.9 በኩባንያው ስም የክፍያ ትዕዛዞችን ፤ ቼኮችን፤ ሀዋላዎችን፤ የሽያጭና የግዥ ውሎችን በኩባንያው መመሪያ መሰረት ይፈርማል፡፡ እንዲሁም የግምሩክ ዲክላራስዮኖችን፤ የገቢ ግብር ማስታወቂያዎችን፤ ሌሎችንም ማመልከቻዎችና ደብዳቤዎች ይፈርማል፤ ያወጣል፤ ያስተላልፋል፡፡

1.10 በዓለም ዓቀፍና በአገር ውስጥ በሚኖሩት እንቅስቃሴዎች ፤በፍርድ ቤቶች ፤ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ፤ በከተሞች አስተዳደርና ክልል መሥሪያ ቤቶች፤ በግል ድርጅቶች እንዲሁም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚገኙ ሦስተኛ ወገኖች ፤በመድን ሰጪ ኩባንያዎች፣ በባንኮች ወይም በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፡፡

1.11 የጠለፋ ዋስትና ውሎች ከመፈረማቸው በፊት ስለውሉ ሁኔታ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

1.12 ሥልጣኑን እንደአስፈላጊነቱ ለኩባንያው የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንዲሁም ወኪሎች፤ ደላላዎች ፤ ጠበቆች ይሾማል/ይወክላል/፡፡ ኩባንያውን ወክሎ መክሰስ ወይም መከራከርና መልስ መስጠት፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ባለሙያ/ጠበቃ/ነገረ ፈጅ/ መወከል ይችላል፡፡

1.13 የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያስተላልፈው ውሳኔ መሰረት ለማህበሩ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአገር ውስጥ ባንኮችና ሌሎች የፋናንስ ተቋማት ገንዘብ ይበደራል፡፡ የባንክ የብድር ማመልከቻዎችንና የብድር ውሎችን በማህበሩ ስም ይፈርማል፡፡ እንዲሁም የኩባንያውን ንብረቶች ለኩባንያው ዕዳ በዋስትና ያስይዛል፡፡

1.14 የኩባንያውን የሥራ እንቅስቃሴ በአግባቡ ለማስተዳደር ፤ ለመቆጣጠርና ለመምራት አስፈላጊ የሆኑትን ማናቸውንም ሌሎች ተግባራት ሁሉ ይፈጽማል፡፡

1.15 በሕግና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ በተደነገጉት እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ሒሳቦች ያቋቁማል፡፡

1.16 የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወስነውና በማህበሩ ዓላማዎች ክልል መሰረት የማህበሩን ገንዘብ በሥራ ላይ ያውላል፡፡ በቦርዱ ሲፈቀድ ከአክስዮን ማህበራት አክስዮን ይገዛል ወይም ይሸጣል፡፡ አክስዮን ማህበራትን ያቋቁሟል፡፡

1.17 በኩባንያው የአሠራር መመሪያ መሰረት የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት ለመግዛት፤ ለመሸጥ፤ ለመከራየትና ለማከራየት የሚያስችሉ ውሎችን በማህበሩ ስም መዋዋል ይችላል፡፡

1.18 ለኩባንያው ስራ አስፈላጊና አስተማማኝ የሆነ የኢንፎርሜሽን ሲስተም በማዘጋጀት እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፡፡

1.19 በኩባንያው የአሠራር መመሪያ መሰረት ኩባንያው በሰጠው የመድን ሽፋን መሰረት አደጋ ደርሶባቸው የተረከባቸውን ንብረቶች፣ ጉዳት የደረሰባቸው ወይም በእርጅና ምክንያት መወገድ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶች እና ከኩባንያው መደበኛ ስራ ጋር በተገናኘ ሌሎች

የኩባንያው የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲሸጡ ወይም እንዲወገዱ ይወስናል፡፡

1.20 የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በዋስትና በመያዝ የመድን ዋስትና ሽፋን ለመስጠት ይችላል፡፡

1.21 በመመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ ያቀርባል፣

1.22 በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ወይም በሕግ ተለይተው የተሰጡ ሌሎች ስራዎች ያከናውናል፡፡

2. ዋና ሥራ አስፈጻሚው በተለይ የሚከተሉትን በሚመለከት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሀ. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎች በወቅቱ በማጠናቀቅ የማህበሩን የሒሳብ ሚዛን እና የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ ማዘጋጀት፤

ለ. ተገምጋሚ የሚሆነውን ያለፈውን የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ አርቅቆ ማቅረብ፤

ሐ. ለቦርዱ ስብሰባዎች ከቦርዱ ሰብሳቢና የማህበሩ ጸሃፊ ጋር በመመካከር አጀንዳ ማዘጋጀት፤ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የዳይሬክተሮችን ቦርድ ስብሰባዎች ማዘጋጀት፤

መ. በአጠቃላይ በዚህ ሰነድ በተለይ ያልተጠቀሱም ቢሆን ለማህበሩ ሥራና ለዓላማዎቹ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች በኩባንያው የአሠራር መመሪያ መሰረት ማከናወን፤

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

### አንቀጽ 39፡ <u>የማህበሩ ፀሐፊ</u>

**1.** የማህበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡

**2.** የፀሐፊው ተጠሪነት ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 40 የማህበሩ ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

የማህበሩ ጸሃፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አሉት፡፡

1. የማህበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ ፤
2. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፤
3. ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤
4. የባለአክስዮኖችንና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤
5. ቃለ ጉባዔዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤
6. በቦርዱ የተወሰኑትን ውሳኔዎች መከታተልና ለቦርዱ ሪፖርት ማቅረብ፤

7. በዋና ሥራ አስፈጻሚው እና በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## የማህበሩ ኦዲተሮች( ተቆጣጣሪዎች)

### አንቀጽ 41፡ የማህበሩ ኦዲተሮች

1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸው ገለልተኛ የውጭ ኦዲተሮች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ፡፡
2. ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ ሃያ በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች እራሳቸው የመረጡትን የውጭ ኦዲተር መሾም ይችላሉ፡፡
3. የኦዲተሮች የስራ ዘመን የሶስት በጀት አመት ሒሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ድረስ ይሆናል፡፡
4. የኦዲተሮች የስራ ዋጋ ክፍያ በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡
5. ኦዲተሮች በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በኩባንያው የሥራ በታዎች በመገኘት ማናቸውንም የምርመራና የቁጥጥር ሥራ ያደርጋሉ፡፡ ለምርመራ ሥራቸው አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑበትን ውሎችን፤ ስምምነቶችን፤ የሒሳብ መዛግብትንና ቃለጉባኤዎችን በአጠቃላይ የኩባንያውን እንቅስቃሴዎች ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን ሁሉ እንዲቀርቡላቸው በመጠየቅ ምርመራ ያከናውናሉ፡፡
6. ማናቸውም አይነት የባለአክስዮኖች ጉባኤ ሲደረግ ኦዲተሮች መገኘት አለባቸው፡፡
7. ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የኩባንያውን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ተገቢውን አስተያየት ይሰጣል፡፡
8. የኩባንያው ሒሳቦች ሲቀርቡለት ጉባኤው ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
9. ለባለአክስዮኖች እንዲከፋፈል ስለቀረበው የትርፍ ድርሻ አስተያየት ያቀርባል፡፡
10. የኩባንያውን ሒሳቦች በሚመረምርበትና በሚቆጣጠርበት ወቅት ያጋጠመውን ሕገ ወጥ የሆኑ ተግባራት ለዳይሬክተሮች ቦርዱና ለባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያስታውቃል፡፡
11. የኦዲተሮች ተግባርና ሃላፊነት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 348 – 354፣ በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የማህበሩ ሒሳብ

### አንቀጽ 42 ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፤ የሒሳብና የመዛግብት አያያዝን በተመለከተ የወጡ ሕጎች የደነገጉዋቸው በማህበሩ ሒሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ላይ ተፈጻሚ ናቸው፡፡

### አንቀጽ 43 ሒሳብና ዓመታዊ ሪፖርት ዘገባ

1. የማህበሩ የበጀት ዓመት እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ያበቃል፡፡
2. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ማብቂያና ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 29(11) መሰረት ለሚቀርበው ሪፖርት /ዘገባ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፡-

ሀ. ዝርዝር የንብረት ቆጠራና የንብረትና የዕዳ ግምት ያዘጋጃል፡፡

ለ. ኩባንያው በእያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት መዝጊያ ላይ የኩባንያውን የሀብትና ዕዳ ሚዛን፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፤ በተጨማሪም ማህበሩ ባለፈው የበጀት ዓመት ኩባንያው ስላደረገው የሥራ ዕንቅስቃሴና አጠቃላይ የሥራ ይዘትና የነበሩት ጉዳዮች የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያሳይ ዘገባ ያዘጋጃል፡፡

ሐ. ዘገባው ስለትርፍና ኪሳራ ሒሳብ እና ስለኦዲተሮች ክፍያ( የሥራ ዋጋ) ዝርዝር መረጃና እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዓመታዊ ትርፍ አደላደል ሃሳቦችን ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 44 ሒሳቦችንና ሪፖርት(ዘገባ) ለኦዲተሮች ማቅረብ

የንብረት ቆጠራ የሒሳብ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት( ዘገባ) ለዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ጥሪው ከመላኩ ቢያንስ ከ40 ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች መቅረብ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 45 የሒሳብ ሚዛንና የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ መግለጫ ይዘት

የሒሳብ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ መግለጫና እንዲሁም የዕዳ ክፍያና የእርጅና የዋጋ ቅነሳ ሒሳቦች መግለጫ አዘገጃጀት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) ድንጋጌዎችንና በየጊዜው ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አስር

## ተፈላጊ ዋና ገንዘብ (ካፒታልና) መጠባበቂያ ሒሳብ ስለመያዝ

## አንቀጽ 46 ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ስለመያዝ

1. ማህበሩ በማናቸውም ጊዜ ፡-

ሀ. ሕጋዊ መጠባበቂያ ሒሳብ ይኖረዋል፡፡ ይህም ዓመታዊ የትርፍ ክፍያ ድርሻ ከመገለፁ አስቀድሞ ከዓመቱ ትርፍ ላይ ታክስ ተነስቶለት ከሚቀረው የተጣራ ትርፍ ላይ አስር በመቶ(10%)ያላነሰ ገንዘብ በመቀነስ የሚጠራቀም ነው፡፡ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፍ ማህበሩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚይዘው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ለ. ያልተከፋፈለ ትርፍ የተያዘና ሌሎች መጠባበቂያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

2. በመሰረቱ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሒሳብ መቀነስ ወይም በመያዣነት መያዝ አይኖርበትም፡፡ ሆኖም የማህበሩን ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ ከፍ ለማድረግ ዓላማ ሲባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቅነሳውን ዝርዝር ሁኔታዎች አስመልክቶ አስቀድሞ በሚሰጠው ፈቃድና መመሪያ መሰረት ብቻ የማህበሩን መጠባበቂያ ሒሳብ መቀነስ ይቻላል፡፡
3. ኩባንያው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለእያንዳንዱ የኢንሹራንስ የውል ዓይነት የተለያዩ መጠባበቂያ ሒሳቦች መያዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ 47 ልዩ መጠባበቂያ ገንዘብ

ማህበሩ፡-

1. በዳይሬክተሮች፤ በማናቸውም ሥራ አስኪያጅ/ዋና ሥራ አስፈጻሚ/ በምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤ በመምሪያ ኃላፊ ወይም በማንኛውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ቸልተኝነት ወይንም ዕምነት ማጉደል ለሚደርስ ኪሳራ መሸፈኛ የሚሆን ልዩ መጠባበቂያ ገንዘብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት መጠን ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሳራ ለመዳን ሲል በዚሁ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደዚህ ዓይነት ከመሰለ ኪሳራ የሚያድን ዋስትና በመስጠት ሥራ ላይ ከተሰማራ የመድህን ድርጅት ዋስትና ሊገባ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 48 መጠባበቂያዎች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 47 ከተደነገገው በተጨማሪ ማህበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚጠብቀውን ለማሟላት በሚያስችለው መጠን ለሚከተሉት የሚውሉ መጠባበቂያዎች ይይዛል፡፡

1. ቢያንስ በዓመት የሚሰላ ሆኖ የአገልግሎት ዘመንን መሰረት ያደረገ የንብረት የእርጅና ዋጋ ቅነሳን፤ የተከማቸ የእርጅና ዋጋ ቅነሳንና ያልተከፈሉ ወይም ያልተሰረዙ ወይም አጠራጣሪ ዕዳዎችን ጨምሮ ለመሸፈን የሚሆን፤
2. ሥራ ለሚካሔድበትና ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ፤
3. ከማደራጀት ወይም የንግድ ሥራ ሽያጭን ወይም የማህበሩን መልካም ስም ከማስፋፋት ከማቋቋሚያ ኮሚሽንና የአክስዮኖችን ዋስትና ጭምር ለመክፈያ፤
4. በማናቸውም ሕግ መሰረት የተገቡ ግዴታዎችን በዋስትና ወይም በመያዣ ለማረጋገጥ የተሰጡ ንብረቶቹን ዋጋ ለመሸፈን የሚውል ሂሳብ፤ ይህ የሚደረገው ግን ግዴታዎቹ ( ተዛማጅነት ያላቸው ግዴታዎች ጭምር) ማህበሩ ስለካፒታልና ስለመጠባበቂያ ገንዘብ የሚፈለጉበትን ሕጋዊ መለኪያዎች ማሟላቱን ለማረጋገጥ ሲባል ከተደረገው ስሌት ውስጥ ያልተቃለሉ ከሆኑ እና

የንብረቶቹም በዋስትና ወይም በመያዣነት መሰጠት ማህበሩ ሊያገኛቸው የማይችልበትን ውጤት አስከትሎበት የሕዝብ ዕዳዎቹን እንዳይወጣ የሚያደርገው ሲሆን ነው።

5. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪዎች ለሚገለጹ ጉዳዮች ወጪ መሸፈኛ።

### አንቀጽ 49 የሒሳብ ሚዛን መግለጫዎችን ስለመላክ

1. የጸደቀው የማህበሩ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ አንድ ቅጅ እንዲሁም ጉባኤው መግለጫውን ያጸደቀበት ውሳኔ ቃለጉባኤ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫው በጸደቀ በ30 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የመንግስት አካል መላክ አለበት።
2. ማህበሩ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች ሪፖርቶችን፣ ለባለአክስዮኖች የሚያቀርበውን ሪፖርት ትክክለኛ ቅጂ፣ እንዲሁም የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ቃለጉባኤ ትክክለኛ ቅጂ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## መፍረስና ሒሳብ መጣራት

### አንቀጽ 50 ለማህበሩ መፍረስ የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተመለከቱት ስለኩባንያዎች መፍረስና ሒሳብ ማጣራት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በኩባንያው ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. ከላይ የተጠቀሰው ማህበሩን የማፍረስና ሒሳብ የማጣራት ሥልጣንና ተግባር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተደነገገው መሰረት ይከናወናል።
3. ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ለማህበሩ መፍረስና ሂሳብ መጣራት በቂ ይሆናል።

   ሀ. ማህበሩን የተቋቋመበትን ዓላማ ሲፈጽም ወይም ለመፈጸም ሳይችል ሲቀር፤

   ለ. ማህበርተኞች የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲስማሙና በቅድሚያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን በማስፈቀድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በፈቃደኝነት ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤

   ሐ. ማህበሩ የአስተዳደር አካላት የሌሉት በመሆኑ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፡

   መ. የባለአክስዮኖች ቁጥር በሕግ ከተፈቀደው በታች ሲሆን ፤

   ሠ. የማህበሩ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን ፤

   ረ. ማህበሩ የዋና ገንዘቡን ሦስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣና በዚሁ ምክንያት የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን።

   ሰ. ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት ማህበሩ እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ሲወሰን

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ደንቦች

### አንቀጽ 51 በመመሥረቻ ሰነድ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች

1. በሕግ በሌላ ሁኔታ እስካልተወሰነ ድረስ የመመስረቻ ሰነዱ የሚሻሻለው በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ/ ስብሰባ/ ነው፡፡

## አንቀጽ 52 የማህበሩን ዋና ገንዘብ ስለማሳደግ

1. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሳይፈቅድ የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ አይቻልም፡፡
2. የማህበሩ ዋና ገንዘብ አዲስ አክስዮኖችን በማውጣት ወይም የነባር አክስዮኖችን ዋጋ በመጨመር ማሳደግ ይቻላል፡፡
3. የአዲስ አክስዮኖች ዋጋ በሚከተሉት መንገዶች ሊከፈል ይችላል፡፡

   ሀ. በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት፤

   ለ. ማህበሩ ያሉበትን የመክፈያ ጊዜያቸው የደረሰ ዕዳዎች በአክስዮን በማቻቻል፤

   ሐ. መጠባበቂያ ወይም ማህበሩ ሊያዝባቸው የሚችሉ ሌሎች ገንዘቦችን ወደ ዋናው ገንዘብ በመጨመር፤

   መ. የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክስዮን በመለወጥ፤
4. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ ዋና ገንዘብ እንዲያድግ የሚያሳልፈው ውሳኔ በአምስት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
5. የማህበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደጉ ሁኔት በንግድ ሕግ አንቀጽ 442-461 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይከናወናል፡፡

## አንቀጽ 53 አክስዮን ለመግዛት መፈረምን ስለማስታወቅ

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ማረጋገጥና በሰነድ እንዲያዙ ማድረግ አለበት፡፡

1. አዲስ አክስዮኖች በሙሉ ለመገዛት መፈረማቸውን፤
2. ከአክስዮኖቹ ዋጋ መከፈል ያለበት ገንዘብ መከፈሉን፤
3. እንዲጨመር የተወሰነው የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መጨመሩን፤ እና
4. በተጨመረው የማህበሩ ዋና ገንዘብ መሰረት የመመስረቻ ጽሁፉ መሻሻሉን፡፡

## አንቀጽ 54 በዓይነት መዋጮ የዋና ገንዘብ/ካፒታል/ መጨመር(ማሳደግ)

1. የማህበሩ ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የዓይነት መዋጮ የሚከፈል ከሆነ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 260፣ 261 እና 262 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 55 የዋና ገንዘብ/የካፒታል/ መቀነስ

1. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር የማህበሩን ካፒታል መቀነስ አይቻልም፡፡
2. የማህበሩ ዋና ገንዘብ ቅነሳ ከተደረገ በንግድ መዝገብ መመዝገብ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣና በማህበሩ ድረ-ገጽ መውጣት አለበት፡፡

3. የማህበሩን ዋና ገንዘብ መቀነስ የሚቻለው፡-

3.1 በአክስዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመቀነስ ወይም

3.2 ነባር አክስዮኖችን አነስተኛ ቁጥር ባላቸው አዲስ አክስዮኖች በመለወጥ ነው፡፡

4. ከካፒታል ቅነሳ ጋር የተያያዘ የጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔዎች የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለው)) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት ይፈጸማሉ፡፡

## አንቀጽ 56 የሀብትና ዕዳ የሒሳብ መግለጫን በማስታወቂያ ስለማውጣት

1. የጸደቀው የማህበሩ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ አንድ ቅጅ እንዲሁም ጉባኤው መግለጫውን ያጸደቀበት ውሳኔ ቃለጉባኤ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫው በጸደቀ በ30 ቀናት ውስጥ በማህበሩ ድረ-ገጽ ላይ መውጣት አለበት፡፡
3. ማህበሩ የሒሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የኦዲተሩን መግለጫ አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ማውጣት አለበት፡፡

## አንቀጽ 57 የማህበሩ የሥራ ዘመን

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ 58፡ <u>ተፈጻሚ ሕግ</u>

1. ይህ መመስረቻ ጽሑፍ በመድን ሥራ አዋጅ፣ ከኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ይፈጸማሉ፡፡
3. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጹት ጉዳዮች ሁሉ ለሴቶችም ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በማህበሩ ውስጥ ባለአክስዮን፤ ዳይሬክተር፤ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤ ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ/፤ የመምሪያ ወይም የዋና ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ለመሆን የሚያስፈልገውን መስፈርት እስካሟሉ ድረስ ሊከለከሉ አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 59፡ <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የወጣው የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበሩት በኩባንያው መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ ይጠናቀቃሉ፡፡

## አንቀጽ 60 <u>መመስረቻ ጽሁፉ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመስረቻ ጽሁፍ በብርሃን ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክስዮኖች አራተኛው አስቸኳይ ጉባኤ ዛሬ ታህሣሥ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ጸድቋል:: በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ታይቶ ሲፈቀድና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አጀንሲ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና እና ተፈፃሚ ይሆናል፡፡